# ተገዶ ከዚህ
# ሃገር መባረር እና
# የመኖሪያ ፍቃድን
# በተመለከተ
# መረጃዎች
# ፤ የጥንቃቄ
# ማሳሰቢያዎች እና
# መጪ ዕድሎች

Bayerischer
Flüchtlingsrat

# የጽሑፉ ይዘት


1. መግቢያ 3

2. ከዚህ በመቀጠል የተጠቀሱትን ግለሰቦች አይመለከትም 4

3. በመሰረቱ ከዚህ በመቀጠል የተጠቀሱትን ግለሰቦች ይመለከታል 7

4. ፓስፖርት ወይንም የልደት ሰርቲፊኬት የሌላቸው ግልሰሰቦች ተገደው እንዲወጡ ማድረግ ይቻላል? 9

5. እኔን አስገድዶ ለመመለስ ግጅት እየተደረገ ከሆነ ምን አይነት ምልክቶችን በጥንቃቄ መገንዘብ አለብኝ? 10

6. የጥገኝነት ማመልከቻዬ ተቀባይነት ባያገኝም ፡ የመኖር መጨ ዕድል አለኝን? 11

7. ምን አይነት አማራጭ ዕድሎች እና ምክረ ሃሳቦችን መገንዘብ አለብኝ? 17

8. ሕጋዊ የመኖር መብት ለሁሉም – ሕገ ወጥ የሚባል ሰው የለም! 20

# 1. መግቢያ

የጅምላ ጥረዛ እና አስቀድመው ይሚደረጉ የቀጠሮ ማሳወቂያዎች ብዙ ግዜ እኔንም አስገድደው ሊመልሱኝ ይሆን  በሚል ሃሳብ ለከፍተኛ ፍራቻ እና እለመረጋጋት ይመራሉ። ስለዚም ፡ ምን አይነት ግለሰቦችን ተገደው ከዚህ ሃገር እንዲወጡ ለመደረግ አደጋ የተጋለጡ መሆናቸውን እና አለመሆናቸውን በዚህ ለማብራራት እንፈልጋለን።

በዚህ የጥንቃቄ ማስገንዘቢያ ጽሁፍ፡ የጥገኝነት ጠያቂዎችን መብት በተመለከት ማብራሪያ ለመስጠት እና በተወሰነ ደረጃ ተገድጄ ልባረር ይሆን በሚል የሚያድርባቸውን ስጋት ለመቀነስ እንሞክራለን፡፡  በጣም አስፈላጊ የሆነው፡ አንድ ግለሰብ በእርግጥ ተገዶ ከዚህ ሃገር እንዲወጣ ለመደረግ አደጋ ተጋልጧል ወይስ አልተጋለጠም የሚለውን ማብራራት ነው። መልሱ አዎን ከሆነ፡ እንደየሁኔታው ሕጋዊ አማራጮችን በመጠቀም ፡ ይግባኝ በማለት የተጋረጠውን ተገዶ የመባረር አደጋ ማስቀረት ይቻላል። ስለዚህም ፡ ጠበቃዎችን ወይም የምክር አገልግሎት ወደሚሰጡ ተቋማት በመሄድ ምክር መጠየቅ አስፈላጊ ነው። ሌላ ተጨማሪ እና ጥሩ ድጋፍ ሊያደርጉላችሁ የሚችሉ፡ በጎ ስድራጊ አጋዦች፣ ጓደኞች፣ ትምህርት ቤቶ ወይንም የስራ ቀጣሪዎ ሲሆኑ ይችላሉ። ብዙ ግንኙነት ያለዎት ከሆነ በበለጠ ጠቃሚ ነው።

እባክዎትን ይህንን ያስተውሉ፡- ይህ ንድፈ ሃሳብ እንጂ ሙሉ ዝርዝር ማብራሪያ አይደለም ፡ እንዲሁም አንድ በሕግ ባለሙያ ጠበቃ  ወይንም በምክር አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ፡ ስለ መኖሪያ ፍቃድ ሕጋዊ ሂደት የሚሰጥን ምክር አይተካም።

# 2. ከዚህ በመቀጠል የተጠቀሱትን ግለሰቦች አይመለከትም

**ፖለቲካ ጥገኝነት መብት የተሰጣቸው እና በስደተኝነት መብት ተቀባይነት ያገኙ**

(በግዜያዊ የፍቃድ ወረቀት ወይንም የመኖሪያ ፍቃድ በ አንቀጽ § 25 ምዕራፍ 1 እና 2 1ኛ ሃረግ የመኖሪያ ፍቃድ ሕግ መሰረት): ፍጹም ተገደው የመባበር ስጋት ሊያድርባቸው አይገባም። ለ 3 ዓመታት የሚያገለግል የመኖሪያ ፍቃድ ይሰጣቸዋል፡ እንዲሁም በደንቡ መሰረት ይራዘምላቸዋል። ከ 5 ዓመታት በኋላ ፡ አስፈላጊው ቅድመ ሁኔታዎች ከተሟሉ፡ ገደብ የሌለው የመኖሪያ ፍቃድ ሊሰጣቸው ይችላል።

**መለስተኛ ጥገኝነት መብት የተሰጣቸው እና ተገዶ ከመባረር በሚከለክል አንቀጽ መሰረት ተገን ያገኙ**

(በግዜያዊ የፍቃድ ወረቀት ወይንም የመኖሪያ ፍቃድ በ አንቀጽ § 25 ምዕራፍ 2 1ኛ ሃረግ እንዲሁም § 25 ምዕራፍ 3 የመኖሪያ ፍቃድ ሕግ መሰረት): እንዲሁም ተገደው የመባረር ስጋት ሊያድርባቸው አይገባም። መጀመሪያ ለ 1 ዓመት የሚያገለግል የመኖሪያ ፍቃድ ይሰጣቸዋል፡ እንዲሁም በደንቡ መሰረት ይራዘምላቸዋል። ከ 5 ዓመታት በኋላ ፡ አስፈላጊው ቅድመ ሁኔታዎች ከተሟሉ፡ ገደብ የሌለው የመኖሪያ ፍቃድ ሊሰጣቸው ይችላል።

**የጥገኝነት ጥያቄ ማመልከቻ አስገብተው ጉዳያቸው እየታየ ያለ ስደተኞች**

(በግዜያዊ የመቆያ ወረቀት ያላቸው): ማመልከቻቸው ተመርመሮ የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚያገኝ ተገደው እንዳይባረሩ ሕጉ ይከለክላል። ከፌደራሉ ቢሮ ቀባይነት ያለማግኘት ውሳኔ ከተወሰነባቸው እና ደንዳቤው ደርሷቸው ይግባኝ ሳይሉ ግዜው ካለፈባቸው፡ ተገዶ የመባር እርምጃ ሊወሰድባቸው ይችላል። ማመልካቻዎን አልተቀበልንም የሚል ውሳኔ ሲመጣ፡ በፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት ይቻላል። እዚህ ላይ የተሰውን የግዜ ገደብ ማክበር የግድ አስፈላጊ ነው።

**የጥገኝነት ማመልከቻቸው እየተመረመረ ያለ የቤተሰብ አባላት**

፡ የግል ቤተሰብ አባላትን በተመለከተ ጉዳዩ የሚታይለት የቤተሰብ አባል ማመልከቻቸው ገና እየተመረመረ ያለ ከሆነ እና ግዜያዊ የመቆያ ወረቀት ያለው ከሆነ፡ ወደ ትውልድ ሃገራቸው በአጣዳፊ ተገደው የመባረር አደጋ እያሰጋቸውም። ከቤተሰቡ አባላት ውስጥ አንዱ የመኖሪያ ፍቃድ ኖሮት ጉዳዩ ግን እየታየ ካለ፡ ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ልጆች፣ ለአቅመ አዳም ያልደረሱት ልጆቹ ወላጆች ፣ ወይንም ይትዳር ጓደኖች በደንቡ መሰረት፡ ተገደው አይባረሩም። ለተሻለ መረጃ እና ጥርጣሬዎን ለማወገድ እባክዎትን ሕጋዊ የምክር አገልግሎት ወደሚሰጥበት ቦታ ወይንም ወደ ጠበቃ ሄደው የምክር አገልግሎት ያግኙ።

**የጥገኝነት ማመልከቻቸው ውድቅ ተደርጎባቸው ለፍርድ ቤት ይግባኝ ያሉ ግለሰቦች፡**

(በቀጣይነት የግዚያዊ የመቆያ ወረቀት ያላቸው): ማመልከቻቸው ብፍርድ ቤቱ ተመርመሮ የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚያገኝ ተገደው እንዳይባረሩ ሕጉ ይከለክላል። ግርድ ቤቱም የይግባኝ ማመልከቻቸውን ውድቅ ካደረው እና ውሳኔው ጸንቶ ከተጠናቀቀ፡ ተገዶ የመባር አደጋ ሊያጋጥማቸው ይችላል። በፍርድ ቤት የሚካሄደው

የይግባኝ ሂደት ውሳኔ ሳያገኝ ቢያንስ ቢያንስ እስከ አንድ አመት ሊቆይ ይችላል።
ለጥንቃቄዎ: ለሁለተኛ ግዜ የጥገኝነት ጥያቄ አቅርበው ከፌደራሉ ቢሮ ተቀባይነት ባለማግኘቱ ይግባኝ ካሉ ወይንም የመጀመሪያ ማመልከቻው ሆኖ "ሕጋዊ መሰረት የሌለው" በሚል አሉታዊ ውሳኔ የተሰጠበት ወይንም "" የማይፈቀድ"" በሚል (ይህ የዱብሊን ስምምነት 3ን ይመለከታል)ማመልከቻዎ ውድቅ ስለተደረገ: ይግባኝ ያሉ ከሆነ: የይግባኝ ማመልከቻዎ በቀጥታ ተገዶ ከመባበር አይታደግዎትም! እነኚህ ግለሰቦች ተገደው ሊባበሩ ይችላሉ: ሌላው አማራጭ ፍርድ ቤቱ በአጣዳፊ ውሳኔ እንዳይባረሩ የሚከለክል ፍርድ ከሰጠ (ትግበራን ማዘይገት) ብቻ ነው። እባክዎትን ሕጋዊ የምክር አገልግሎት ወደሚሰጥበት ቦታ ወይንም ወደ ጠበቃ ሄደው የምክር አገልግሎት ያግኙ።

## ከቤተሰብ ተለይተው የተሰደዱ ለአቅመ አዳም / ሄዋን ያልደረሱ ታዳጊዎች:

ተገደው የመባረር አደጋ እያሰጋቸውም። ቢሆንም ግን ዕድሜያቸው ለአቅመ አዳም / ሄዋን በደረሱ ግዜ: የመኖሪያ ፍቃዳቸው ተመልሶ ሊሰረዝባቸው ይችላል (የ 18 አመት ልደታቸው ሲደርስ ለአቅመ አዳም/ ሄዋን ደርሰዋል)። ለአቅመ አዳም/ሄዋን ደርሰዋል በደረሱ ግዜ: ከዚህ ሃገር ተገዶ የመባረር አደጋ ተመልሶ ሊጋረጥባቸው ይችላል። እባክዎትን በግዜ ሕጋዊ የምክር አገልግሎት ወደሚሰጥበት ቦታ ወይንም ወደ ጠበቃ ሄደው የምክር አገልግሎት ያግኙ።

## ነፍሰ ጡር እና በእናትነት እንክብካቤ ግዜ ያሉ እናቶች (ከመውለዳቸው በፊት 6 ሳምንት :

እና ከወለዱ በኋላ 8 ሳምንት): ይህንን በተመለከተ የውጭ ዜጎች ጉዳይ ጽሕፈት ቤት ማስረጃ ካለው። አስፈላጊ ከሆነ Mutterpass የሚባለውን ደብተር ወይንም የእናቶች ሓኪም ማስረጃን ማቅረብ። በጤና አደጋ ላይ ያሉ ነፍሰ ጡር እናቶች: የእንክብካቤ ግዜያቸው ባይደርስም ተገደው እንዳይባረሩ የሚከለክል ወረቀት ሊሰጣቸው ይችላል። ይህም የሚሆነው የሓኪም ማስረጃ ካቀረቡ እና ተገደው እንዳይባረሩ የሚከለክል የመኖሪያ ፍቃድ እንዲሰጣቸው ካመለከቱ ነው።

## በሙያ ስልጠና ላይ ያሉ እና Ausbildungsduldung የሚባል ወረቀት ያላቸው ተማሪዎች

(በ አንቀጽ § 60c AufenthG መሰረት ወረቀት ያላቸው): የጥገኝነት ማመልከቻቸው ተቀባይነት ያላገኘ ግለሰቦች ብቃት ያለው የሙያ ስልጠና ላይ የሚገኙ ከሆነ እና „Ausbildungsduldung" የሚባል ወረቀት ያላቸው ከሆነ: ተገደው ከዚህ ሃገር እንዳይባረሩ ሕጉ ይከለክላል። ማሳሰቢያ: „Ausbildungsduldung" የሚባለው ወረት ሳይኖራቸው በሙያ ስልጠና ላይ ያሉ ግለሰቦች: ተገደው የመባረር አደጋ ሊጋረጥባቸው ይችላል።

## ለስራ ተብሎ የሚሰጥ Beschäftigungsduldung የሚባል ወረቀት ያላቸው ግለሰቦች

(በ አንቀጽ § 60c AufenthG መሰረት) : ይህ ወረቀት እስካላቸው ድረስ : ተገደው ከዚህ ሃገር እንዳይባረሩ ሕጉ ይከለክላል። ይህ ለስራ ተብሎ የሚሰጥ ዱልዱንግ በመሰረቱ አንድ ግዜ እስከ 30 ወራት እንዲያገለግል ሊሰጥ ይችላል። ከዚያም በሁዋላ የስራ ዱልዱንግ የሚባለው ወረቀት: ይራዘማል ወይንም ወደ የመኖሪያ ፍቃድነት እንዲቀየር ማመልከት ይቻላል።

## በሕጋዊ ጉዳይ ምክንያት ዱልዱንግ የሚባል ወረቀት ያላቸው ግለሰቦች

: እንዲሁም ተገደው ከዚህ ሃገር እንዳይባረሩ ሕጉ ይከለክላል። ሕጋዊ ምክንያት ማለት፤ በጤ እክል ምክንያት

መጓዝ አለመቻል፣ የቤተሰብ ምክንያት፣ በትምሕርት ላይ መገኘት። እነኚህን ምክንያቶች በተመለከተ፡ ለውጭ ዜጎች ጽሕፈት ቤት፡ ተሐኪም  የማስረጃ ሰነዶችን ፣ የጋብቻ ማስረጃ፣ የትምሕርት የምስክር ወረቀት፡ ወ.ዘ.ተ ማቅረብ ተገቢ ነው። ይህ ሕጋዊ ጥበቃ የሚተገበረው፡ ያቀረቡት ማስረጃ ከተመረመረ እና ተቀባይነት ካገኘ በኋላ ብቻ ነው ።

**ተግባራዊ ምክር:** የትናው አይነት ዱልዱንግ እንዳለዎት በእርግጠኝነት የማያውቁ ከሆነ፡ ጉዳይዎትን የሚያስተናግደውን የውጭ ዜጎች ጽሕፈት ቤት፡ በደብዳቤ ይጠይቁ፡ ወይንም ወደ ጠበቃ ወይንም ወደ ምክር አገልግሎት የሚሰጥበት ቦታ ይሂዱ።

**የመኖሪያ ፍቃድ ያላቸው ግለሰቦች (ለምሳሌ የመኖሪያ ፍቃድ በ አንቀጾች §§ 18a, 18b, 19c, 19d, 25a, 25b, 25 Abs. 5 oder 23a የመኖሪያ ፍቃድ ሕግ መሰረት)**

፡ ተገደው እንዳይባረሩ ሕጉ ይከለክላል። መጀመሪያ ለ 1 ዓመት የሚያገለግል የመኖሪያ ፍቃድ ይሰጣቸዋል፡ ከዚያም በመቀጠል ማመልከቻ ሲያስገቡ፡ በደንቡ መሰረት ይራዘምላቸዋል። ከ 5 ዓመታት በኋላ ፡ ገደብ የሌለው የመኖሪያ ፍቃድ ሊሰጣቸው ይችላል።

# 3. በመሰረቱ ከዚህ በመቀጠል የተጠቀሱትን ግለሰቦች ይመለከታል

በመሰረቱ : ከዚህ በመቀጠል የተጠቀሱት ግለሰቦች ተገዶ ለመባረር አደጋ የተጋለጡ ናቸው። የውጭ ዜጎች ጉዳይ ጽሕፈት ቤት አስገድዶ ከዚህ ሃገር ለማስወጣት ሲወስን : ሁል ግዜ የግል ጉዳይን በተናጠል በማጣራት ነው። ይህም ማለት ሁሉም ማለት ሁሉም ግለሰቦት አጣዳፊ በሆነ ተገዶ የመባረር አደጋ ላይ አይደሉም ማለት አይደለም፡ ምንም ጥርት ካላደረጉ፡ በሃሳብ ደረጃ መቸም ቢሆን በሃይል ተገደው ሊባረሩ ይችላሉ።

## ከዚህ ሃገር እንዲወጡ ግዴታ ተጥሎባቸው ያሉ ግለሰቦች

በመሰረቱ ተግደው ከዚህ ሃገር እንዲወጡ የመደረግ አደጋ የሚያሰጋቸው ግለሰቦች፡ የጥገኝነት ማመልከቻቸው ተቀባይነት ያላገኘበት ውሳኔ በፍርድ ቤት የተጠናቀቀ። ይህም ማለት በ አንቀጾች §§ 60a ወይንም 60b የመኖሪያ ፍቃድ ሕግ መሰረት፡ እንዲሁም የድንበር ማለፊያ የሚባል ከዚህ ሃገር እንዲወጡ ቀነ ገደብ የተጣለበት ወረቀት የተሰጣቸው፡ ወይንም ምንም አይነት ወረቀት ያልተሰጣቸው ናቸው። ከሁሉም በላይ መጠንቀቅ የሚያስፈልገው : የውጭ ዜጎች ጉዳይ ጽሕፈት ቤት ምንም አይነት ወረቀት ካልሰጠዎት ወይንም “ተቀባይነት የሌለው/ungültig“ የሚል ማሕተም እዱልዱንግ ላይ ከተመታብዎት ፣ የስራ ፍቃድዎ መልሶ ከተነጠቀ፣ በኢምባሲ ወይንም የቆንሱላ ጽሕፈት ቤት ቀጠሮ ከተያዘልዎት፣ ወይንም እዚህ ቦታ መጥተው ቃለ መጠቅ ይደረግልዎታል የሚል ደብዳቤ ከመጣልዎት ነው። እባክዎትን የምክር አገልግሎት በሚሰጥበት ቦታ ወይንም ወደ ጠበቃ በመሄድ ምክር፡ ያግኙ።

## ለረጅም አመታት ዱልዱንግ ይዘው ከዚህ ሃገር እንዲወጡ ግዴታ ተጥሎባቸው ያሉ ግለሰቦች፡

ከነኚህ አብዛኞዎቹ፡ ተገደው ከዚህ ሃገር እንዲወጡ ለማድረግ አደጋ የተጋለጡ ናቸው፣ የጥገኝነት ጥያቄ ማመልከቻቸው ከአመታት በፊት ውድቅ ከተደረገ በኋላ ዱልዱልግ ተሰጥቷቸው የሚኖሩ። እዚህ ሃገር ለረጅም አመታት ኑረዋል፡ በአብዛኛው ስራ ይሰራሉ እንዲሁም ቤት ተከራይተው ነው የሚኖሩት። አብዛኛዎቹ ለአመታት ከጠበቃዎች እንዲሁም ከበጎ ፍቃድ አድራጊዎችም ሆነ የምክር አገልግሎት ሰጪዎች ጋር ግንኙነት የላቸውም:: እነኚህ ግለሰቦች በአስቸኳይ የመኖሪያ ፍቃድ እንዲሰጣቸው ማመልከት አለባቸው፡ ቅድመ ሁኔዎችን የሚያሟሉ ከሆነ (ቁጥር 6ን ይመልከቱ ተገዶ ከመመለስ ምን ይከላከለኛል? - የጥገኝነት ማመልከቻዬ ተቀባይነት ባያገኝም : የመኖር መጪ ዕድል?)

## የጥገኝነት ማመልከቻቸው፡ ምንም ምክንያታዊ ያልሆነ („offensichtlich unbegründet“) በሚል ውሳኔ ውድቅ የተደረገባቸው ግለሰቦች፡

ይህንን አይነት ያለመቀበል ውሳኔን በተመለከት : ይግባኝ ለማለት የሚሰጠው አጭር የቀነ ቀጠሮ ገደብ ነው፡ እንዲሁምይግባኝ ማለት ብቻ : ተገዶ ከመባረር የሕጋዊ ጥበቃ ዋስትና አያሰጥም። ይህ ሊደርስባቸ የሚችል ግለሰቦች፡ ለምሳሌ በአብዛኛው፡ ሕግ ይከበርባቸዋል ከሚባሉ ሃገራት የመጡ አመልካቾችን ነው። የግድ ወደ ጠበቃ ወይንም የምክር አገልግሎት በሚሰጥበት ቦታ በመሄድ ምክር፡ያግኙ ።

**አስገድዶ ለመሸነት ዝግጅት የሚደረግ እስራትን በሚመለከት ማሳሰቢያ፡**

በሚያሳዝን ሁኔታ፡ አሁኑ ወቅት ከዚህ ሃገር እንዲወጡ የተጠየቁ ስደተኞችን፡ ለማሰር ለባለ ጉዳዩ መስሪያ ቤት መንገዱ ቀላል ሁኗል። አንድ ግዜ ከታሰሩ በኋላ፡ ከቤተሰብ ጋር መገናኘት ፣ ጓደኞችን ማግኘት፣ ወይንም ጠበቃ መቅጠር በጣም አስቸጋሪ ነው።

እኛ በበኩላችን፡ አስፈላጊ የሆኑ ስልክ ቁጥሮችን (ለምሳሌ፡ የጠበቃን፡ ወይንም ሌላ የሚያምኑትን ግለሰብ) በአንድ ልዩ ወረቀት ላይ ጽፈው፡ ለብቻው እንዲይዙ እንመክራለን፡ በቁጥጥር ስል በዋሉ ግዜ፡ ተንቀሳቃሽ ቴሌፎንዎ ይወሰድብዎታል፡

ለበጎ ፍቃደኛ ደጋፊዎች፡ አደጋው ከተጋረጠበት ግለሰብ የውክልና ደብዳቤ ስልጣን መያዝ፡ ምናልባት በቁጥጥር ስር በዋለ ግዜ ለማገዝ በጣም አስፈላጊ ነው።

# 4. ፓስፖርት ወይንም የልደት ሰርቲፊኬት የሌላቸው የጥገኝነት አመልካቾች ተገደው እንዲወጡ ማድረግ ይቻላል?

አዎን፣ ወደ ተወሰኑ ሃገራት፡ ፓስፖርትም ሆነ የልደት ማስረጃ ወረቀት የሌላቸውን ግለሰቦች አስገድዶ መመለስ ይቻላል። እነኚህ ሃገሮች ከጀርመን መንስት ጋር፡ ወይንም፡ ከአውሮፓ ህብረት መንግስታት ጋር፡ የጋራ ስምምነት ፈርመዋል። እንደዚህ አይነት ስምምነቶች፡ ጥገኝነት ጠያቂዎችን ያለምንም አይነትፓስፖርት የማንነት የልደት ማስረጃ አግደድዶ ለመመለስ ሁኔታውን ምቹ ያደርጋሉ። የተወሰኑ ሃገሮች፡ በጀርመን ሃገር ካሉ የውጭ ዜጎች ጉዳይ ጽሕፈት ቤት ባለስልጣናት ጋር ሆነው የግለሰቦችን ማንነት የማጣራት ስራን ያጋሂዳሉ። ከዚያም በሁዋላ ጥገኝነት ጠያቂዎችን አስገድዶ ለመመለስ የሚያስችል ፍቃድ ወረቀት የመስጠት እና ያለመስጠቱ ሁኔታ ፡ የጥገኝነት ጠያቂዎቹ ሃገሮች ለትብብር ባላቸው ዝግጁነት ብቻ ላይ የተመሰረተ ነው።

ማንነትን በማረጋገጥ ሂደት ላይ ተግባራዊ ምክር፡ ማንነትን ማረጋገጥ በሁሉም አይነት የመኖሪይ ፍቃድን ሕግ በሚመለከቱ ሂደቶች በጣም አስፈላጊ ነው። የጥገንነት ጥያቄ ማመልከቻዎ እየተመረመረ በሚገኝበት ወቅት ፡ ወደ ትውልድ ሃገርዎት ኤምባሲ በመሄድ ፓስፖርት እንዲሰጥዎት ማመልከት፡ የለብዎትም እይገደዱምም። ይሁን እንጂ፡ ማመልከቻዎ እየተመረመረ ባለበት ወቅትም ቢሆን መንነትዎን ለማረራገጥ ቢቻል ደግም የልደት ማስረጃ ለማግኘት ጥረት ማድረግ አስፈላጊ ነው፡ ፡ እዚህ ላይ ያደረጉትን ጥረት በሙሉ ለማስረጃነት ጽፈው ማቆየቱ እናም አስፈአጊ ሆኖ ከውጭ ዜጎች ጉድይ ጽሕፈት ቤት በተጠየቁበት ወቅት ያደረጉትን ጥረት ለማሳወቅ እንደማስረጃነት ለማቅረብ ያግዝዎታል። ለውጭ ዜጎች ጉዳይ ጽሕፈት ቤት፤ ማነቱን በተመለከት ቃሉን ሲሰጥ የሃስት መረጃን የሰጠ ግለሰብ፡ የግድ የምክር አገልግሎት የሚሰጥበትን ተቋም ወይንም ጠበቃ ማማከር አለበት። አብዛኘኛዎቻችሁ  ማንነታችሁ እንዶረጋገጥ ማሰረጃዎችን ወይንም ፓስፖርት ማውጣት፡ ተገዳችሁ ወደ ሃገራችሁ እድትመለሱ የሚደረገውን ሂደት በራሳችሁ ትብብር ማፋጠን እንድሆነ ስለምትረዱ፡ ፍርሃት አለባችሁ። በሌላ ወገን ደግሞ፡ የመንነት ማስረጃ ወረቀትን አለማውጣት፡ የመኖሪያ ፍቃድ በመስጠት ሂደት ላይ እንቅፋት ሊሆን የሚችልበትም ሁኔታ አለ። እባክዎትን ይህንን በተመለከተም የምክር አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን ወይንም ጠበቃ ያማክሩ።

# 5. እኔን አስገድዶ ለመመለስ ግጅት እየተደረገ ከሆነ ምን አይነት ምልክቶችን በጥንቃቄ መገንዘብ አለብኝ?

ለውጭ ዜጎች ጉዳይ ጽሕፈት ቤት: ጥገኝነት ጠያቂዎችን አስገድዶ የመመለስ ሂደት: በጣም ብዙ ግዜ የሚፈጅ ከመሆኑም በላይ  ብዙ ወጪም ይጠይቃል። ስለዚም በተለምዶው እንደሚደረገው: በመጀመሪያ ግለሰቦች በፍቃደኝነት ይህንን ሃገር ለቀው እንዲወጡ ጥረት ይደረጋል። ጉዳዩ የሚመለከተው ግለሰብ በተወሰነ ግዜ ውስጥ በፍቃደኝነት ከዚህ ሃገር ካልወጣ: በተለያዩ መንገዶች ጫና ይደረግበታል: እንዲሁም ፓስፖርት እንዲያመጣ እና በፍቃደኝነት ይህንን ሃገር ለቆ እንዲወጣ ማሳመን ይሞከራል።የውጭ ዜጎች ጉዳይ ጽሕፈት ቤት: ግን በዚሁ ወቅት ከበስተጀርባ በድብቅ የፓስፖርት መተኪያ ሰነዶችን በማውጣት ይህንን ግለሰብ አስገድዶ ለመመለስ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። በባየርን ክልል ውስጥ: ይህንን ጉዳይ የሚያስፈጽመው አካል: ላንደስ አምት ፍዩር አዝዩል ይባላል: እንዲሁም በየዞን አስተዳደር ውስጥ የሚገኙ : ማእከላዊ የውጭ ዜጎች ጉዳይ ባለስልጣን ጽሕፈት ቤቶች : ከዚህ እንዲወጡ የተገደዱትን ይገኝነት ጠያቂዎች : ከዚህ ሃገር ለማስወጣት ከፍተኛ ጥረት ከሚያደርጉት ዋናዎቹ ናቸው። ይገኝነት ተገን እማግነት የተደረገ ማመልከቻ ተቀባይነት ሳያገኝ ከቀረ: በሚኖሩበት ቦታ ያለው የውጭ ዜጎች ጽሕፈት ቤት የአመልካችን ማሕደር በአብዛኛው ወደ: ማእከላዊው የውጭ ዜጎች ባለስልጣን ያስተላልፋል። ይሄኛው መስሪያ ቤት የተሻለ አቅም ስላለው የጥረዛውን ዝግጅት የፈጽማል። አንዳንዴም ሊያጋጥም እንደሚችለው: እዛው ከሚኖሩበት ቦታ ባለው የውጭ ዜጎች ጉዳይ ጽሕፈት ቤት በኩል ብቻ የተጠረዙ ግለሰቦችም አሉ።

**ይህንን የማስጠቀቂያ መልእክት በጥብቅ ሊገነዘቡት ይገባል እንዲሁም በአስቸኳይ ወደ ምክር አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ወይንም ጠበቃ በመሄድ ምክር መውሰድ አለብዎት:**

- የሚሰጥዎት በርሃዊ ክፍያ እንዲጎድል ከተደረገ
- ፓስፖርት የለዎትም በሚል ብቻ ክስ ከተመሰረተብዎት
- ከሚኖሩበት ቦታ ርቀው እንዳይዘዋወሩ የመንቀሳቀስ ገደብ ከተጣለብዎት -ችበሚኖሩበት የከተማ ወይንም ወረዳ አስተዳደር ውጥ ብቻ እንዲዘዋውወሩ ከታዘዘ-
- በሃገርዎ ኤምባሲ ወይንም የሃገርዎ መግስት ተወካይ በሚገኝበት ሌላ ቦታ ማንነትዎን ለማታጣራት በሚል እንዲሄዱ ቀጠሮ ከተያዘልዎት
- የተሰጠዎት ዱልዱንግ የግዜ ገደብ  በጣም አጭር ለሆነ ግዜ ብቻ ከተራዘመልዎት (አንዳንዴም ለጥቂት ቀናት ብቻ)
- የስራ ፈቃድዎ መልሶ ከተሰረዘ
- የዱልዱንግ ወረቀትዎ ሙሉ በሙሉ ከተወሰደብዎት ወይንም „ungültig“  የሚል ማህተም ካረፈበት
- የድንበር መሻገሪያ ነጭ ወረቀት ከተሰጠዎት
- ምንም አይነት መቀሳቀሻ ወረቀት ካልተሰጠዎት
- የውጭ ዜጎች ጉዳይ መስሪያ ቤት ሰራተኛ በግልጽ: በቅርቡ ወይንም በቀጣይ ቀናት በግዳጅ ሊሸኙ ነው ካሉዎት

# 6. ተገዶ ከመመለስ ምን ይከላከለኛል? - የጥገኝነት ማመልከቻዬ ተቀባይነት ባያገኝም ፡ የመኖር መጪ ዕድል አለኝን?

ምንም እንኳን ያቀረቡት የጥገኝነት ማመልከቻ ተቀባይነት ስላጣ አሉታዊ መልስ የተሰጠው ቢሆንም፡ ለረጅም ዘመናት ዱልዱንግ በሙባል ወረርቀት ለኖሩ ግለሰቦች የመኖሪያ ፍቃድ የማግነት አማራጭ እድል አለ። ይህንንም ለማድረግ ምንግዜም እርስዎ በግልዎ ለውጭ ዜጎች ጉዳይ ጽሕፈት ቤት ማመልከቻ ማስገባት አለብዎት። እባክዎትን ይምክር አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን ወይንም ጠበቃ ያማክሩ።

**በመኖሪያ ፍቃድ ሕግ ቁጥር § 25a AufenthG መሰረት ለታዳጊዎች እና ለአቅመ ቅዳም እና ሄዋን ለደረሱ ወጣቶች ፡ የመኖሪያ ፍቃድ ፡**

ማናቸው ጥገኝነት ጠያቂዎች፡ ከ3 አመታት በላይ ያለማቋረጥ ፡ ማመልከቻ ባስገቡበት ግዜ የሚሰጥ የግዜያዊ መንቀሳቀሻ ወረቀት፣ ዱልዱንግ ወይንም የመኖሪያ ፍቃድ ይዘው በጀርመን ሃገር የኖሩ እና እድሜያቸው ከ 14 እስከ 27 ድረስ ከሆነ፡ አንድ በዚህ ሃገር ውስጥ በጥሩ ሁኔታ ተዋህደው ለሚኖሩ የውጭ ታዳጊዎች እና ለአቅመ ቅዳም እና ሄዋን ለደረሱ ወጣቶች የሚሰጥ የመኖሪያ ፍቃድ እንዲሰጣቸው ማመልከት ይችላሉ። እነርሱም ለ 3 ዓመታት ትምህርት የተማሩ፡ ወይንም ተምህርታቸውን/ የሙያ ስልጠና ለማጠናቀቃቸው መረጃ ያላቸው መሆን አለባቸው። ማንነታቸው የተረጋገጠ እና ማመልከቻውን በሚያስገቡበት ግዜ፡ ፓስፖርት ያላቸው መሆኑ የበለጠ ጠቃሚ ነው። እንዲሁም፡ ምንም አይነት ትኩት ሊሰጠው የሚችል ጥፋት ፈጽመው በወንጀለኝነት የተቀጡ ሊሆን አይገባውም።

ከዚህም በተጨማሪ፡ ቢያንስ ቢያንስ ለ 12 ወራት ዱልዱንግ ያላቸው መሆነ አለበት (ያስተውሉ፡- በ § 60 b AufenthG መሰረት ማንነታቸው ላልተረጋገጠ ግለሰቦች፡ የተሰጠ ዱልዱንግ መሆን የለበትም )። ዕድሜያቸው ከዚህ በታች የሆኑ ሕጻናት እና ልጆች፤ በወላጆቻቸው ወይንም ታዳጊ ወጣት ወንድም እና እህቶቻቸው ምክንያት የመኖሪያ ፍቃድ የማግኘት ዕድል አላቸው።

**በመኖሪያ ፍቃድ ህግ § 25b AufenthG መሰረት ለአዋቂዎች የሚሰጥ የመኖሪያ ፍቃድ:**

ማናቸውም ጥገኝነት ጠያቂዎች፡ ከ 6 ዓመታት በላይ (ብቻቸን ለሚኖሩ) ወይንም ከ 4 ዓመታት በላይ (ለአቅመ አዳም/ ሄዋን ያልደረሱ ልጆች ላሏቸው ወላጆች)፡ ባለማቋረጥ ማመልከቻ ባስገቡበት ግዜ የሚሰጥ የግዜያዊ መንቀሳቀሻ ወረቀት፣ ዱልዱንግ ወይንም የመኖሪያ ፍቃድ ይዘው በጀርመን ሃገር የኖሩ እና በዚህ ሃገር ውስጥ በጥሩ ሁኔታ ተዋህደው የሚኖሩ ከሆነ ፡ የመኖሪያ ፍቃድ እንዲሰጣቸው ማመልከት ይችላሉ።

ይህም እንዲፈቀድልዎት ፓስፖርት ማቅረብ አለብዎት፡ የኑሮ ወጪዎን በራስዎ ገቢ የመሸፈን አቅም ሊኖርዎትም ፡ ይገባል እንዲሁም የጀርመን ቋንቋ ችሎታ ማስረጃ (A2) ማቅረብ አለብዎት። በተወሰኑ ሁኔታዎች ላይ ለሚገኙ ግለሰቦች በልዩ ሁኔታ አስተያየት ሊደረግላቸው ይችላል፡ እነዚህ ግለሰቦች ፡ ሙሉ የኑሮ ወጪያቸውን ለመሸፈን ላይገደዱ ይችላሉ። ለምሳሌም፡- አንድ ወላጅ ብቻውን ሁኖ ልጅ ማሳደግ፣ ወይንም ስራ ለመስራት

የማያስችል የጤና እክል ያለባቸውን ይመለከታል። ይህንን በተመለከት አንድ የምክር አገልግሎት የሚሰጥን ተቋም ወይንም ጠበቃ ያማክሩ። ምንም አይነት ጥፋት ሰርተው ፡ ሁሉን በሚመለክት ወንጀል ከ50 ቀናት በላይ ወይንም ፡ ጥገኝነት ጠያቂዎችን ብቻ በሚመለከት ወንጀል (ለምሳሌ፡ ፓስፖርት ለምን አላመጣህም ተብሎ) ከ 90 ቀናት የበለጠ የእስራት መተኪያ የሚሆን የገንዘብ ክፍያ ቅጣት፡ ያልተቀጡ ሉሆኑ ይገባል።

**በመኖሪያ ፍቃድ ሕግ § 104c AufenthG መሰረት ይሚሰት የመኖሪያ ፍቃድ የማግኘት ዕድል:**

- ማናቸውም የጥገኝነት መብት አመልካቾች እዚህ ሃገር ከመጡበት ቀን ጀምሮ እ.ኤ.አ እስከ ፡ ቀን 31/ 10 /2022 ያለ ምንም ማቋረጥ አዚህ ሃገር ተቀምጠው አምስት ዓመት የሞላቸው ከሆነ እና በዚም ቆይታቸው፡ ማመልከቻ ባስገቡ ግዜ በተሰጣቸው ግዜያዊ መንቀሳቀሻ ወረቀት ወይንም ዱልዱንግ ወይንም የመኖሪያ ፍቃድ ይዘው የኖሩ ከሆነ ፡ ለ 18 ወራት የሚቆይ የመኖሪያ ፍቃድ እንዲሰጣቸው ማመልከት ይችላሉ፤ ማመልከቻውን በሚያስገቡበት ሰዓት ግን ዱልዱንግ ያላቸው ሊሆኑ ይገባል ። ይህ ውሳኔ በ አንቀጽ § 60b AufenhtG መሰረት ፡ ማንነታቸው ላርተረጋገጠ ግለሰቦች የሚሰጥ ዱልዱንግ ያላቸውንም ይመለከታል። ቢሆንም ግን ምንም አይነት ጥፋት ሰርተው ፡ ሁሉን በሚመለክት ወንጀል ከ50 ቀናት በላይ ወይንም ፡ ጥገኝነት ጠያቂዎችን ብቻ በሚመለከት ወንጀል (ለምሳሌ፡ ፓስፖርት ለምን አላመጣህም ተብሎ) ከ 90 ቀናት የበለጠ የእስራት መተኪያ የሚሆን የገንዘብ ክፍያ ቅጣት፡ ያልተቀጡ ሉሆኑ ይገባል።

**ተግባራዊ ምክር:-** የተለያዩ ተመኖሪያ ፍቃድ አይነቶችን ለማግኘት ቅድመ ሁኔታ ከሆኑት አንዱ፡ ጉዳዩ የሚመለከተው ግለሰብ እዚህ ሃገር ብቻ በመቀመጥ ሳያቋርጥ ግዜያዊ የመንቀሳሰሻ ወረቀት፣ የመኖሪያ ፍቃድ ወይንም ዱልዱንግ ሲኖራቸው ይገባል። ብዙ ግዜ ምንም አይነት ዱልዱግም ያልተሰጣቸው ግለሰቦች አሉ። የውጭ ዜጎች ጉዳይ ጽህፈት ቤት ለነኚህ ግለሰቦች የድንበር መሻገሪያ ወረቀት ይሰጣቸዋል፡ ወይንም ሌላ አይነት የማንነት ማረጋገጫ ወይንም ምንም አይነት ወረቀት ላይሰጣቸውም ይችላል። ብብዙ አጋጣሚዎች እንደየሁኔታው፡ የውጭ ዜጎች ጉዳይ ጽሕፈት ቤት የመኖሪያ ፍቃድ ሊከለክል ይችላል። ስለዚም እንደየሁኔታው፡ ዱልዱንግ የሚባለው ወረቀት እንዲሰጥዎት መጠየት እና ከዛም ፍርድ ቤት ሄዶ ይግባኝ ማለት ተገቢም ሊሆን ይችላል። ይህ ግን በተጨባጭ ሊሳካ የሚችለው፡ ጉልዱንግ ሊያሰጡ የሚችሉ ቅድመ ሁኔታዎች ከተሟሉ ብቻ ነው። እባክዎትን፡ የምክር አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም እይንም ጠበቃ ያማክሩ።

**የጥገኝነት ተገን እዲሰጥዎት አዲስ ማመልከቻ ማስገባት :**

- ምናልባት አዲስ የጥገኝነት ማመልከቻ ለማስገባት በቂ ምክንያንት መኖሩን እና አለመኖሩን፡ ጠበቃዎች ይህንን ጉዳይ ሊያጣሩልዎት ይችላሉ፡፡ አዲስ የጥገኝነት ማመልከቻ ለማስገባት ቅድመ ሁኔታው፡ ከአሁን በፊት ለጥገኝነት ተገን ባመለከቱበት ወቅት በማመልከቻዎ ውስጥ ከተዘረዘሩ ምክንያቶቹ፡ ሌላ በጨባጭ የተቀየረ አዲስ ምክንያት ሊሆን ይገባዋል። ከነዚህም ለምሳሌ፡ ሕመም፣ ህይማኖትን መቀየር፣ አዲስ የተፈጠረ ግብረሰዶማዊነት፣ ከዚህ በፊት በሴቶች የጾታ አካል ላይ ተድርጎ የነበረ ግርዛትን/ አካል ማጉደል፡ ላይ መልሶ ቀዶ ጥገና የማድረግ ወይንም አዲስ ማስረጃ መገኘት። እንዲሁም በትውልድ ሃገሮ ላይ የከፋ አዲስ ሁኔታ መፈጠር፣ ለዚህም በቂ ማስረጃዎች ካሉ፣ ይህንን ለአዲሱ የጥገኝነት ጥያቄ ማመልከቻ እንደማስረጃነት ማቅረብ ይቻላል።

**ተግባራዊ ምክር:-** ለውጭ ዜጎች ጉዳይ ጽሕፈት ቤት፡ ስለ ህመምዎ ማሳወቅ፣ የሙያ ስልጠና የሚጀምሩ ከሆነ፣ ትዳር የፈጸሙ ከሆነ፣ ነፍሰ ጡር ከሆኑ፣ ሊወልዱ ግዜዎ የደረሰ ከሆነ እንዲሁም ከህዝባዊ አገልግሎት እየሰጡ ያለ ከሆነ፡ ለምሳሌ በበጎ አድራጊነት የሚሰሩ ከሆነ፡ የቋንቋ ትምሕርት እየተከታተሉ ከሆነ፡ ማሳወቅ በጣም አስፈላጊ ነው። ብዙ ግዜ እንደሚያጋጥመው፡ ባለስልጣን መስሪያ ቤቶቹ በጣም አስፈላጊ እና አስገድዶ ከመባረር ሊያድንዎት የሚችሉ ተጨባጭ ሁኔታዎችን፡ ሳያውቁ የቆዩ ሊሆን ይችላል።

## በሙያ ስልጠና ላይ ለሚገኙ የሚሰጥ ዱልዱንግ:-

የጥገኝነት ማመልከቻቸውን በተመለከተ፡ አሉታዊ ውሳኔ የተሰጠባቸው እና በጥገኝነት መመከቻቸው እየተመረመረ ባለበት ወቅት የሙያ ሥልጠና ጀምረው ያሉ ስደተኞች በሙሉ ፡ በሙያ ስልጠና ለይ ለሚገኙ አመልካቾች በአንቀጽ 60c መሰረት ለጊዜው ከአገር ከመባረር የሚከለክል የመቆያ ፍቃድ የማግኘት መብት አላቸው። ይህም አውስቢልዱንግስ ዱልዱንግ በመባል የሚታወቀው ፍቃድ ለሥልጠናው ጊዜ የሚጸና ከመሆኑም በላይ በዚህ ጊዜ ከአገር ከመባረር ዋስትና ይሰጣል ። ከአሉታዊ የጥገኝነት ማመልከቻ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላም ቢሆን ፡ ይሙያ ስልጠና መጀመርና ለጊዜያዊ የሀገሪቱ መቆያ ወረቀት እንደሰጥዎ ማመልከት ይቻላል ። ይሁን እንጂ የኢሚግሬሽን ባለ ሥልጣናት ብዙውን ጊዜ እምቢ ስለሚሉና ይህ ሊሆን የሚችለው ከአገር ማመከቻዎ በአሉታዊ ፍርድ ተጠናቆ ወደ ዱልዱንግ ከመግባትዎ በፊት ለሦስት ወራት አስቀድሞ መሆን ስለነበረበት ይህ ይበልጥ አስቸጋሪ ነው። በዚህ ወቅት እርስዎን ከአገር ለመባረር ዝግጅት ማድረግ ይጀምራሉ። የሙያ ስልጠናው በተሳካ ሁኔታ ከተጠናቀቀ በኋላ የመኖሪያ ፈቃድ በመኖሪያ ፍቃድ ሕግ ቁጥር 19d መሰረት እንዲሰጥዎ ማመልከት ይቻላል። ከመጋቢት 2024 ጀምሮም ተያያዥ መስፈርቶች ከተሟሉ በመኖሪያ ፍቃድ ሕግ ቁጥር 16 g መሰረት የስልጠና የመኖሪያ ፈቃድ የሚባለው እንዲሰጥዎ ማመልከት ይቻላል። አውስቢልዱንግስ ዱልዱንግ የሞባለው ወረቀት ያለው ማንኛውም ሰው ስለዚህ ጉዳይ ከምክር አገልግሊት ሰጪ ማዕከሎች ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ይኖርበታል።

## በ § 16g AufenthG መሰረት ፡ የሙያ ስልጠና ላይ ላሉ የሚሰጥ የመኖሪያ ፈቃድ:-

ከመጋቢት 1 ቀን 2024 ዓ.ም ጀምሮ ከሀገር የመውጣት ግዴታ ያለባቸው ግን የሙያ ስልጠና ላይ የሚገኙ ግለሰቦች በአዲሱ የመኖርያ ፍቃድ ሕግ ቁጥር 16g መሰረት የመኖሪያ ፈቃድ ለማግኘት ማመልከት የሚችሉ ይሆናል። ቅድመ ግዴታዎቹም ፡ ልክ የሙያ ስልጠና ላይ የሚገኙ ግለሰቦች እንደሚሰጠ ዱልዱንግ አይነት ነው፡ ይህም ብቃት ያለው የሙያ ስልጠና ማግኘት እና የራስን ወጪ ለመሸፈን የመቻል ሁኔታ እንዲሁም ፓስፖርት የማምጣት ግዴታን መወጣት የሚችሉ ናቸዉ።

በተራ ቋንቋ ፡- አንድ የራሱም ወጪዎች ሁሉ በራሱ መሸፈን የቻለ እና ፓስፖርት ያለው ፡ ይህንን በ አንቀጽ § 16g AufenthG፣ መሰረት የሚሰጠውን የመኖሪያ ፍቃድ ፡ ማግኘት ይችላል፤ ይህን ማሟላት ያልቻለ ፡ በስልጠናው ዱልዱንግ ውስጥ ይቀራል።

## ለስራ ተብሎ የሚሰጥ ግዜያዊ መቆያ ወይንም ዱልዱንግ:

-ለስራ ተብሎ የሚሰጥ ግዜያዊ መቆያ ወይንም ዱልዱንግ፡ ማለት በመኖሪያ ፍቃድ ሕግ አንቀጽ § 60d መሰረት ፡ ከዚህ ሃገር የመውጣት ግዴታ ላለባቸውና ለረጅም ጊዜ ሲሰሩ ለቆዩ ሰዎች ተገዶ ላለመባረር

ዋስትና ለመስጠት የታሰበ ነው። ለስራ ተብሎ የሚሰጥ ግዜያዊ መቆያ ወይንም ዱልዱንግ ለመሰጠት ቅድመ ሁኔታው፡ እስከ ቀን፡ 31/12/2022 እዚህ ሃገር የገቡ ከሆኑ ነው። በተጨማሪም ሙሉ የማህበራዊ ዋስትና ክፍያዎችን የሚከፍል ስራ ሳላፋት 12 ወራት የሰራ ፡ ይኑሮ ወጪውን በሙሉ በራሲ ሊሸፍን የሚችል ፣ እንዲሁም ቢያንስ ለ12 ወራት ዱልዱንግ የነበረውና በቂ የጀርመንና ቋንቋን የመናገር እውቀት ያለው እንዲሆን ይጠበቅበታል። የሥራው ውል በሳምንት ቢያንስ 20 ሰዓት የሚሠራ መሆን አለበት ። በተጨማሪም ወደ እዚህ ሃገር ከገባበትን ቀን በምመርኮዝ ፡ ማመልከቻውን እስከሚያስገባበት ቀን ወይንም ቢዘገይ እስከ ታህሳስ 31/ 2024 ድረስ ማንነቱ ተጣርቶ መታወቅ አለበት። ተያያዥ የወንጀል ተግባሮችን የፈጸመ መሆን የለበትም። አብዛኛውን ጊዜ የሥራ ፈቃድ ዱልዱንግ የሚሰጠው ለ30 ወራት ነው ።

## ቤተሰባዊ ምክንያቶች - ትዳር እና ልጆች:

- የጀርመን ዜጋ ከሆነ ሰው ወይም የመኖሪያ ፈቃድ ካለው ሰው ጋር መጋባት ፡ እንደየ ሁኔታው ፡ ለግል የመኖሪያ ፈቃድ ሊያስገኝ ይችላል ። በጀርመን ሃገር ልጅ መወለድ በዚሁ ብቻ የመኖሪያ ፈቃድ አያስገኝም ።ከወላጅ አንዱ ወገን የመኖሪያ ፈቃድ ወይም የጀርመን ዜግነት ካለው፡ ይህንን አስታክኮ የመኖሪያ ፈቃድ ማግኘት ይቻላል። እንደየ ሁኔታው የውጭ አገር ዜጎች ጉዳይ ቢሮ አሁንም ከዚህ ሃገር እንዲወጡ ሊጠይቅ ይችላል። ይህም ማለት ሃገርዎ ሆነው የቪዛ ማመልከቻ በማስገባት እዚህ ሃገር ወደ አለው የትዳር ጓደኛዎ ወይም ቤተሰብ እንደገና እንዲዋሐዱ ማስቻል ይኖርብዎታል ማለት ነው። ልዩ እይታ ሊደረግ የሚችለው፡ በአሁኑ ጊዜ ወይም ለመጪው ረጅም ጊዜ ወደ ሃገርዎ መመለስ ምክንያታዊነት የጎደለው ከሆነ ብቻ ነው።

## የሙያ ሥልጠናው ከተጠናቀቀ በኋላ የሚሰጥ የመኖሪያ ፈቃድ:

- በመኖርያ ፍቃድ ሕግ አንቀጽ ቁጥር 19d መሠረት በተሳካ ሁኔታ የጀመሩትን የሙያ ስልጠማ በተሳካ ሁኔታ ካጠናቀቁ ፡ ዱልዱንግ ያላቸው ግለሰቦች ፡ የመኖሪያ ፈቃድ ለማግኘት ማመልከት ይችላሉ። ይህን የመኖሪያ ፈቃድ ማግኘት የሚቻለው ጉልዱንግ ያላቸው ከሆነ እና ከሙያ ብቃትህ ጋር የሚመጣጠን የሥራ ዕድል ካለህ ወይም እየሰራህ ካለህ ብቻ ነው ።

## ህመም/መጓዝ አለመቻል:

-አንዳንድ ጊዜ ከባድና አጣዳፊ ሕመም ፡ ለግዜው መጓዝ ባለመቻል ምክንያት ዱልዱንግ እንዲሰጥ ወይም ተገዶ ከአገር እዳይባረር ዋስትና የሚሰጥ ውሳኔ እንዲወሰን ሊያደርግ ይችላል። ይሁን እንጂ አብዛኛውን ጊዜ የኢሚግሬሽን ባለሥልጣናት ወይም የፌደራሉ ስደተኞች እና ሚግሬሽን ቢሮ ፡ ለሕክምና የምሥክር ወረቀቶች እውቅና አይሰጡም። የህክምና ሰርተፊኬቶች፡ የመኖርያ ፍቃድ ሕግ አንቀጽ § 60ሀ ምዕራፍ 2c ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው። እነዚህ መስፈርቶች በጣም ከባድ ናቸው ። አንዳንድ ጊዜ ተጨማሪ የሕክምና ምርመራ በጤና ቢሮ ሰራተኛ እንዲደረግ ትእዛዝ ይሰጣል። ከዚያም የሕዝብ ጤና ባለሙያው የምርመራው ውጤት ትክክል መሆን አለመሆኑን ያመዛዝናሉ። እባክዎ የምክር አገልግሎት ሰጪ ማዕከል ወይም ጠበቃ ያነጋግሩ።

## ልዩ ችግር አጣሪ ኮሚሽን:

- በጀርመን ከአራት ዓመት በላይ የቆዩ፣ እየሰሩ ወይም በሙያ ስልጠና ላይ ያሉ እና በሚገባ ክህዝቡ ጋር ተዋህደው ያሉ ስደተኞች ፡ ለልዩ ችግር አጣሪ ኮሚሽን (HFK) ጉዳያቸው እንዲታይ ሊቀረቡ ይችላሉ። ይሁን እንጂ ጥንቃቄ መደረጉ ይመከራል፤ ለልዩ ችግር አታሪ ኮሚሽን ጉዳዩ ቢቀርብም፣ አሁንም ከአገር ተገደው

ከመባረር የሚከላከል ነገር የለም። በዚህ ላይ እንደየግለሰብ ጉዳዮች ለየብቻ ላይ መጠየቅ አለበት። ለHFK ከመቀረብ የሚያግዱ ምክንያቶች አሉ። እነኚህም ተያያዥ የወንጀል የፈጸሙ ወንጀሎች፡ እንዲሁም ተገደው እንዲመለሱ ላማድረግ ፡ የሚደረገው ዝግጅት የተጀመረ ከሆነ (ለምሳሌ ለበረራ መመዝገብ) የመሳሰሉ የመሰናዶ እርምጃዎችን መውሰድን ያካትታል። በመኖርያ ፍቃድ ሕግ § 23 AufenthG መሰረት ልዩ ችግር ላለባቸው የመኖሪያ ፍቃድ ከመሰጠቱ በፊት፡ ፓስፖርት መቅረብ አለበት። እንዲሁም ለባቫሪያ መንግሥት ፓርላማ ቀደም ሲል የቀረበ ወይም ውድቅ የተደረገ አቤቱታ ካለም ለልዩ ችግር አጣሪ ኮሚሽኑ ማመልከቻው እንዳይቀርብ የሚከለክል ምክንያት ነው።

## ለክልላዊ መንግሥት ፓርላማ አቤቱታ፡

- በባቫሪያ ክልላዊ መንግስት ፓርላማ ፡ አቤቱታ የማቅረብ እድል አለ። አንድ የጋራ አቤቱታ ማለት፡ ወደ አንድ ፓርላመንት የሚቀርብ እና አንድ የባቫሪያ ባለስልጣን መስሪያ ቤት ውሳኔን በመቃወም ፡ የሚቀርብ አቤቱታ ነው፤ ለምሳሌ በስራ ላይ የሚጣለውን እገዳ ወይም ታቅዶ ያለ ተገዶ ከአገር መባረርን የሚቃወም አቤቱታ ነው። አቤቱታ ለማቅረብ የቀረበው ቅጽ በባቫሪያ ግዛት ፓርላማ ድረ ገጽ ላይ ይገኛል። አቤቱታው ከአገር ከመባረር የሚከላከል መሆን አለመሆኑ የሚመሰረተው በግለሰብ ጉዳይ ላይ ነው ።

## የቤተ ክርስቲያን ጥገኝነት፦

በአደጋ ላይ ያሉ አንዳንድ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን መጠለያ ውስጥ ተቀባይነት ካገኙ በአብያተ ክርስቲያናት ሊገቡ ይችላሉ። ይሁን እንጂ ለቤተ ክርስቲያን መጠለያ የሚሆኑባቸው ቦታዎች ጥቂት ናቸው ። አብዛኛውን ጊዜ ቤተ ክርስቲያናቱ መኖሪያ ፍቃድ ለማግኘት የሚያስችል ሕጋዊ ዋስትና እንዲኖር ይጠይቃሉ፤ ለምሳሌ ከዱብሊን ስምምነት ጋር በተያያዘ፣ የጊዜ ገደብ ማለቁን ይጠይቃል። የሆነ ሆኖ የምታውቃቸውን ምዕመናን አነጋግረህ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትን ጠይቅ ። በዚህ ፡ www.kirchenasyl.de ገጽ ላይ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ሁሉ ታገኛለህ።

## ከዚህ ሃገር መውጣት እና ዳግም መግባት:

- ለአንዳንድ ሰዎች በትውልድ ሃገራቸው ውስጥ ወይም በጎረቤት ሀገር ለአጭር ጊዜ ቆይተው እንደገና ቪዛ ይዘው መግባት ጥሩ አማራጭ ሊሆን ይችላል። በግዳጅ ከዚህ ሃገር መባረር ማስቀረት የማይቻል ክስተት፡ ከሆነ “በፈቃደኝነት“ መውጣት እና ዳግም መግባት የመጨረሻ አማራጭ ሊሆን ይችላል።

ምክንያቱም፡ - ከአገር ከመባረር ጋር በተያያዘ ብዙውን ጊዜ በጣም አሰቃቂ እና አዕምሮን ይሚጎዳ እንደሆነ ማስታወስ ያስፈልጋል ። በተጨማሪም የኢሚግሬሽን ባለ ሥልጣናት ግለሰቦችን ከአገር በጉልበት ካስወጡ በኋላ ወደ አገራቸው ተመልሰው እንዳይገቡ እገዳ ይጥላሉ፤ ይህ እገዳ አብዛኛውን ጊዜ ለበርካታ ዓመታት የሚቆይ ነው። እንደገና ከመግባታቸው በፊት አብዛኛውን ጊዜ ከአገር ለመባረር የሚወጣው ወጪ በተባረረው ግለሰብ መከፈል ይኖርበታል።

ከዚህ ሃገር በገዛ ራስዎ ለመውጣትና እንደገና በቪዛ ተመልሶ ለመግባት ቅድመ ሁኔታዎች ፡ ብቃት ያለው ስራ ወይም የሙያ ስልጠና ማግኘት ፣ ጋብቻ መፈጸም ወይም ልጅ መውለድ ሊሆን ይችላል። በራስ ውሳኔ ከዚህ ሃገር በሚወጣበት ግዜ፡ ከሃገር ከመውጣታቸው በፊት (ቅድመ ፈቃድ ይባላል) ከሃላፊው የኢሚግሬሽን ባለስልጣን ዳግም ለመግባት ስምምነት ማግኘት ጠቃሚ ነው። ቪዛ ይዞ ወደ እዚህ ሃገር ተመልሶ ለመግባት በመሰረቱ፡ የኡሮ ወጪን መሸፈን መቻል፣ የመኖሪያ ቤት፣ የስራ ውል እና የጀርመንኛ ቋንቋ ክህሎት ማስረጃ

ማቅረብ ያስፈልጋል። በአሉበት ሃገር የሚገኘው ኤምባሲ በሃላፊነት ከሚመለከተው እዚህ ሃገር ውስጥ ካለው የኢሚግሬሽን ባለስልጣን ጋር በመመካከር ቪዛውን ይወስናል። እባክዎ የምክር አገልግሎት ሰጪ ማዕከል ወይም ጠበቃ ያነጋግሩ.

## ከ 2024 ጀምሮ ያሉ አዳዲስ ሕገ ደንቦች:

- እነኚህ አዳዲስ ሕገ ደንቦች: በአብዛኛው ሰማያዊ- ካርድ -ኢዩ እንዲሁም : በአንቀጽ §18a እና በ18b በመኖሪያ ፈቃድ ሕግን እና በተለምዶ ከሰብአዊ መብት ኢሚግሬሽን „የመንገድ ለውጥ“ በሚባለውን የሚያደርጉትን ይመለከታል። በተለይም ጥሩ ችሎታ ባላቸው ሠራተኞችና ብቃት ባላቸው የሙያ ሥልጠናን በወሰዱ ግለሰቦች ላይ ይተገበራል። ተጨማሪ መረጃ : በ “GGUA e.V” ድረ ገጽ ላይ ማግኘት ይቻላል። አዳዲስ መረጃዎችን በማግኘት መጠቀም እችላለው ብለው ካሰቡ የምክር ማእከል ይጎብኙ።

**ተግባራዊ ምክር፦** ወንጀል መፈጸም ለብዙ የመኖሪያ ፈቃድ እንዳያገኙ ለመገለል ምክንያት ነው። ማንኛውም ሰው በአጠቃላይ ወንጀል ወይም በመኖሪያ ፍቃድ ሕግ ወይም በጥገኝነት ሕግ (ለምሳሌ በፓስፖርት አለመኖር ወይም በሕገወጥ መንገድ በገባበት ጊዜ) ለተፈጸመው ወንጀል ከ50 ቀናት በላይ ቅጣት ወይም ከ90 በላይ የዕለት ተዕለት ቅጣት የተቀበለ ሰው አብዛኛውን ጊዜ የመኖሪያ ፈቃድ ከማውጣት ይገለላል። አንዳንድ ጊዜ ገደቡ ዝቅተኛ ነው ። ይህም አነስተኛ ቅጣት እንኳ የመኖሪያ ፈቃድ እንዳታገኝ ሊያግድህ ይችላል ማለት ነው ። የቅጣት ትዕዛዝ የተቀበለ ማንኛውም ሰው በአስቸኳይ ወደ ጠበቆች መሄድ ይኖርበታል። ለዚህ ምርጡ ጠበቆች በወንጀል ሕግና በመኖሪያ ፍቃድ ሕግ ላይ የሚሰሩ ናቸው።

# 7. ምን አይነት አማራጭ ዕድሎች እና ምክረ ሃሳቦችን መገንዘብ አለብኝ?

**ጀርመንኛ ቋንቋ ይማሩ:**

- የጀርመንኛ ቋንቋ እና የእውቀት ብቃት ያለው ስራ ለመቆየት እድሉዎ በጣም አስፈላጊ ነው : በጥገኝነት ማመልከቻዎ እየታየ ባለበት ግዜ ውስጥ ያለውን ጊዜ ጀርመንኛ ለመማር መጠቀም፣ የሙያ ብቃት ማረጋገጫዎችን፣ የማንነት ማረጋገጫ ማስረጃዎችን ወይም ስለሕመምው የሐኪም ማስረጃዎችን ማሰባብሰብ አስፈላጊ ነው። የጥገኝነት ማመልከቻዎ በአሉታዊ ሁኔታ ተፈርዶ ከተዘጋ፣ ብዙ ጊዜ ወደ ጀርመን ኮርስ መግባት ወይም የስራ ፈቃድ ማግኘት አስቸጋሪ ነው።

የጥገኝነት ማመልከቻቸው በቀጣይ የማጣራት ሂደት ውስጥ ያሉ ሁሉም ስደተኞች: የውህደት ኮርስ ብቃት ማረጋገጫ ለመማር ማመልከት ይችላሉ። ይህም የውህደት ኮርስ ለመመዝገብ ያስችልዎታል እና ወጪውን የፌደራሉ የስደተኞች እና ሚግሪአሽን ቢሮ ይሸፍናል። የጥገኝነት ማመልከቻዎ በአሉታዊ መልኩ ከተወሰነ ይህ ዕድል ከአሁን በኋላ አይኖርም።

የጥገኝነት ማመልከቻዎ ቀደም ሲል ተቀባይነት ሳያገኝ ከቀረ እና ከአገር መባረራርዎ ለጊዜው ዱልዱንግ የሚባለው ወረቀት ከተሰጠዎት፣ እርስዎ እራስዎ በመክፈል በጀርመንኛ ኮርስ ውስጥ መሳተፍ ይችላሉ። የምክር ማእከልዎን የኮርሱ ወጪ ለእርስዎም ዱልዱንግ ቢኖርዎትም ሊሸፈን ይችል እንደሆነ ይጠይቁ.

በፈቃደኝነት ወይም በሕጋዊ የጀርመንኛ ኮርሶች ላይ የመካፈል አጋጣሚ ካልተገኘ: በራሳችሁ ተነሳስታችሁ እንድትማሩ እናበረታታችኋለን። ለዚህም በርካታ የኢንተርኔት አገልግሎቶችና አፕሊኬሽኖች አሉ።

**ጀርመንኛ ቀደም ብለው በተማሩ ጊዜ የተሻለ ዕድል አለ ። መቼም ዘገየ አይባልም። ዛሬ ይጀምሩ!**

*ሥራ፡-:*

ሥራ ብቻውን ከአገር ከመባረር አይከላከልም። የሆነ ሆኖ የመቆየት መብትን በተመለከተ ለተለያየ አመለካከት ስራ አስፈላጊ ነው (ከላይ ይመልከቱ)።

ማመልከቻ ባስገቡ ግዜ የሚሰጥ መንቀሳቀሻ ወረቀት ያላቸው ጥገኝነት ጠያቂዎች ከ6 ወር (ከ 1/3/2024 ጀምሮ) በኋላ የጥገኝነት ማመልከቻ ውሳኔ ሂደቱ ገና በህጋዊ መንገድ ያልተጠናቀቀ ከሆነ በጀርመን እንዲሰሩ ይፈቀድላቸዋል።

ዱልዱንግ ወረቀት ተሰጥጧቸው : ማንነታቸው የተረጋገጠላቸውና ከስደተኞት የመጀመሪያ መቀበያ ተቋማት

ውጭ የሚኖሩ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ በጀርመን ከ3 ወር የመኖሪያ ቤት ቆይታ በኋላ ፡ በውጭ አገር ዜጎች ጉድይ ቢሮ ፈቃድ እንዲሰሩ ይፈቀድላቸዋል። ግለሰቡን ከዚህ ሃገር አስገድዶ ለማባረር የሚያስችሉ የዝግጅት እርምጃዎች በሂደት ላይ ካሉ ግን ይህ ሊሆን አይችልም ።

የሥራ ፈቃድ ለማግኘት በጽሑፍ ካመለከቱና በጽሑፍ ተቀባይነት ካላገኙ፡ የምክር አገልግሎት ሰጪ ተቋም ወይም ጠበቃ ያነጋግሩ ። ብቃት ያለው ስራ (የሙያ ስልጠና ወይም ከዩኒቨርሲቲ የምስክር ወረቀት ያለው) ያለብቃት ረዳትነት ከስራ የበለጠ ዋጋ ያለው መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ነው። በቋሚነት ጥሩ ችሎታ የሌለው የረዳትነት ሠራተኛ ሆነህ የምትሠራ ከሆነ ቶሎ ሥራህን ልታጣና የምታገኘው ገቢ ሊቀንስ ይችላል። የራስህን መተዳደሪያ ለረጅም ጊዜ አስተማማኝ ለማድረግ ብቃት ያለው ሥራ ብቻ ነው የሚያዋጣው ።

### ድጋፍ ሰጪ ካባቢ ሁኔታ፡

በተቻለን መጠን ጉዳዩ የሚመለከታቸውን፣ ደጋፊዎችን እና ጠበቆችን፡ ለእኛ የታወቁን ፡ ስደተኞችን በጋራ ሰብስቦ የማባረሪያ ቀናት ለማሳወቅ ፡ እና ይህንን አደጋ ላይ ለወደቁ ሰዎች እንዲያስተላልፉ ለመጠየቅ እንሞክራለን። ብዙውን ጊዜ ከአገር ስለመባረሩ ቀን የምናውቀው በአጭር ጊዜ ውስጥ ብቻ ሲሆን ጠበቃ ለመደወል ብዙ ጊዜ አይኖርም ።

ቀደም ባሉት ጊዜያት ስደተኞችን ገብድ ይዞ ለመመለስ በሞመክርበት ቀን በደረሰበት ጊዜ ፡ ፖሊሶች አያገኙዋቸውም ነበር ። ሰዎች ተደብቀዋል ተብለው ሳይከሰሱ፡ ከማረፊያቸው ውጭ ለ3 ቀንና ሌሊት እንዲቆዩ ይፈቅድላቸዋል። ይሁን እንጂ፤ ጥደብቋል ትብላችሁ ከነዋሪነት ከተሰረዛችሁ፡ ራሳችሁን በህግ መከላከል ትችላላችሁ ። የምክር አገልግሎት ማዕከል ወይም ጠበቃ ያነጋግሩ.

ከእርስዎ ጋር አስፈላጊ የሆኑ የስልክ ቁጥሮችን (ለምሳሌ ጠበቃ ወይም በእርስዎ የታመነ ሰው) ሁል ግዜ ከርስዎ እንዳይለይዎ እናበረታታለን። ለደጋፊዎች በአደጋ ላይ በሚገኘው ግለሰብ ስም ማለትም ከባለስልጣናት መረጃ ለማግኘት የተፈረመ የአቃቤ ህግ ውክልና ስልጣን መስጠቱ ጠቃሚ ነው።

### በትምህርት ቤትና በሥራ ቦታ ባህሪ፡

- በሙያ ትምህርት ቤቶችና የሥራ ቦታዎችም ቢሆን ጉዳዩ የሚመለከታቸው ስደተኞች ይፈለጋሉ ። ትምህርት ቤቶች፣ የግል ግለሰቦችም ሆኑ አሠሪዎች ከአገር ለመባረር በሚደረገው ሙከራ ባለ ሥልጣናትን የመደገፍ ግዴታ የለባቸውም። የት እንዳለህ ለባለሥልጣናት ምንም ዓይነት መረጃ መስጠት አያስፈልገህም ።

አንድ ሰው ተግዶ ለመባረር በሚወሰድበት ጊዜ ምን ማድረግ እንዳለበት የሚገልጽ መረጃም እዚህ ላይ ማግኘት ይቻላል፤ https://noborderassembly.blackblogs.org/booklets/

### አስፈላጊ ፦

ከአገር ከመባረር ሙከራ ያመለጠ ማንኛውም ሰው አሁንም አደጋ ላይ ነው። ስለዚህም እዚህ ሃገር የመኖሪያ ፍቃድ አግኝቶ ለመቆየትና ፡ ተገዶ ለመባረር በሚደረግ ዝግጅት ወድ እስር ቤት ለመወሰድ፡ አደጋ ላለመጋለጡ በተቻለ ፍጥነት እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል ።

በጊዜው እርምጃ ውሰድ

አብዛኞቹ የጥገኝነትመብት ጠበቆች ብዙ ደንበኞች አሏቸው። ብዙውን ጊዜ ጠበቆች የደንበኞቻቸውን ጉዳይ ሙሉ በሙሉ መመርመርና የመኖሪያ ፍቃድ ማግኘት እድል እንዳላቸው መገመት አይችሉም ። ለዚህ ነው ለጉዳት የተጋለጡት ግለሰቦች እና ጠበቆች እዚህ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ። አብዛኛውን ጊዜ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሰዎች በጠበቃ በሚገባ የተወከሉ ና/ወይም በሚገባ የተመከሩ ከሆነ በመልካም ጊዜ ማመልከቻ ማቅረብ ይቻል ዘንድ ከአገር ማባረር ሊቆም ይችላል።

## የፖለቲካ ንቁ ተሳትፎ

ምናቸውም በዚህ ፖሊሲ ላይ ዕርምጃ መውሰድ የሚፈልጉ ሰዎች የፖለቲካ ጫና ሊፈፅሙ ይችላሉ፣ ለምሳሌ የአካባቢውን የፓርላማ አባላት በማነጋገር ወይም በሚቀጥሉት ምርጫዎች ላይ ሌሎችም ጉዳዩን ትኩረት እንዲሰጡት በማስገንዘብ ነው። አንዳንድ ጊዜ አንድን ሰው ለመደገፍና ወደፊት ከአገር መባረሩን ለማስቆም የፓርላማ አባላትን ድጋፍ መጠየቅ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ተቃውሞና ሰላማዊ ሰልፍም እንድ አማራጭ ሊሆን ይችላል።

## የአውታረ መረብ ግንኙነቶች

ለአደጋ የተጋለጡ ሰዎችን በተቻለ መጠን መረጃ እንዲያገኙ ለማድረግ፡ ጥሩ የመገናኛ አውታረ መስመር ያስፈልጋል። ድረ ገጹ https://noborderassembly.blackblogs.org/de/abschiebe-alarm/ በቡድን ደረጃ ከአገር የሚባረሩበትን ቀን ይዘረዝራል። ለስደተኞች መብት ተነሳሽነት ካላቸው ጋር ይገናኙ እና ስለ ጅምላ ጥረዛ ቀናት እና ሌሎች አማራጮች ይወቁ። አጠቃላይ መፍትሄ የለም። ከአገር ተገደው እንዳይሰደዱ መከላከል ማለት ፡ ለዘላቂ የመኖር መብት አገኙ ማለት አይደለም። እዚህ ላይ የቀረቡት አማራጭ እርምጃዎች አንድ ላይ ተቀናጅተው ስኬታማ ሊሆኑ ይችላሉ። አብረን እንሞክረው!

# 8. ሕጋዊ የመኖር መብት ለሁሉም – ሕገ ወጥ የሚባል ሰው የለም!

የባቫሪያ የስደተኞች ምክር ቤት ስደተኞችን አስገድዶ ከአገር ማባረርን በጥብቅ ይቃወማል። የስደተኞች መመለስ በነጻነትና በራስ ፍቃድ መወሰን ብቻ መከናወን አለበት። በካምፖች ውስጥ በማረፊያ አማካኝነት ስደተኞችን ማራቅ እና ማግለልን እንቃወማለን እናም ለሁሉም እኩል መብት እንጠይቃለን። ከአንተና ከአንተ ጋር ሆነን ለሁሉም ስደተኞችና ስደተኞች እውነተኛ የመኖሪያ መብት ለማግኘት እየታገልን ነው ።

## አድራሻችን

ቀጠሮ የምንሰጠው በቅድሚያ ቀጠሮ ከያዙ ብቻ ነው። ይደውሉ ወይም ኢ-ሜይል ይላኩ

**ሙኒክ ቢሮ| የባቫሪያ ስደተኞች ምክር ቤት | ዌስትንድስትር 19 | 80339 ሙኒክ | ስልክ 089 -76 22 34 | ፋክስ 089 -76 22 36 | kontakt@fluechtlingsrat-bayern.de**

**የሰሜን ባቫሪያ ቢሮ | የባቫሪያ ስደተኞች ምክር ቤት | Gugelstr. 83 | 90459 ኑረምበርግ | ስልክ 0911 -99 44 59 46 | ፋክስ 0911 - 99 44 59 48 | kontakt@fluechtlingsrat-bayern.de**

Bayerischer
Flüchtlingsrat